የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ
ለንደን
Embassy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia
LONDON

ቀን ፡ ሐምሌ 27 ቀን 2014 ዓ.ም.

ቁጥር ፡ ኢ.ኤም.ለ. 774/4/11/2014

# የምስጋና መልዕክት

## በዩናይትድ ኪንግደም እና ሰሜን አየርላንድ ለምትገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን

የለንደን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲ በዩናይትድ ኪንግደምና ሰሜን አየርላንድ ከሚገኙ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አደረጃጀቶች ጋር በመቀናጀት በአገራችንን በተለይም በአማራና በአፋር ክልል በተከሰተው የጸጥታ ችግር ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች ማቋቋሚያ የገንዘብ ድጋፍ ሲያሰባስብ መቆየቱ ይታወሳል፡፡

በዚህ መሠረት በፈረንጆቹ 2021 ዓመት መጨረሻ አካባቢ በለንደንና በሌሎች የዩኬ ከተሞች ዳያስፖራውን በማስተባበር በተዘጋጁ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች £216,500.26 የገንዘብ ድጋፍ የተሰባሰበ ሲሆን ይህ ገንዘብና የሳምንት ገቢያቸውን ለአገራዊ አጀንዳዎች ድጋፍ ለመለገስ በወሰኑ የዳያስፖራ አባላት የተቋቋመው የሳምንት ገቢዬ ለኢትዮጵያዬ የሚባል ማህበር ያሰባሰበው £75,230.00 በአጠቃላይ £291, 730.26 በክልሎቹ በጦርነቱ ምክንያት ለተጎዱ የጤና ተቋማት መልሶ ማቋቋሚያ እንዲውል በተወሰነው መሠረት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የጤና ሚኒስቴር ተለይተው ለቀረቡ በአፋር ክልል ለሚገኘው ሂዳ የጤና ጣቢያ እንዲሁም በአማራ ክልል ለሚገኙ ወሉዲ የጤና ጣቢያ፣ ሰሪል የጤና ጣቢያ እና አሁንተገኝ የጤና ጣቢያዎች ድጋፍ እንዲደረግላቸው ጥያቄ አቅርቧል፡፡

በዚህ መሠረት አሁንተገኝ ጤና ጣቢያን የሳምንት ገቢዬ ለኢትዮጵያዬ ማህበር ባሰባሰበው £75,230.00 እንዲደገፍ፣ ሌሎቹ 3 ጤና ጣቢያዎች ደግሞ በዩኬ ከተሞች ማለትም ለንደንና አካባቢው፣ ኮቨንተሪ፣ ስቶክ ኦን ትሬንት፣ ማንቸስተር እና ኖቲንግሀም በተዘጋጁ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች የተገኘው £216,500.26 እንዲላከላቸው ክፍፍሉም በጤና ጣቢያዎቹ በሚገለገለው የህዝብ ብዛት እንዲሆን በለጋሾች በተወሰነው መሠረት ክፍፍሉ በሚከተለው መልኩ እንዲሆን በመጠየቅ ኤምባሲው ገንዘቡን የጤና ሚኒስቴር በላከው የባንክ አካውንት ገቢ አድርጓል፡፡

17 PRINCES GATE
LONDON, SW7 1PZ
www.ethioembassy.org.uk
TEL: 020 7589 7212
FAX: 020 7584 7054
e-mail: info@ethioembassy.org.uk

| ተ.ቁ. | የጤና ተቋሙ ስም | የሚገኝበት ክልል | ዞን/ወረዳ | ተጠቃሚ ህዝብ ብዛት | የተለገሰ ገንዘብ መጠን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሂዳ የጤና ጣቢያ | አፋር | - | 24,754 | 59,537.57 |
| 2 | ወለዲ የጤና ጣቢያ | አማራ | ኦሮሚያ ልዩ ዞን | 40,000 | 96,126.12 |
| 3 | ሰሪል የጤና ጣቢያ | አማራ | ሰቆጣ ዙሪያ ወረዳ፣ ዋግምራ ዞን | 25,342 | 60,836.57 |
| 4 | አሁንተገኝ የጤና ጣቢያ | አማራ | አንጎት ወረዳ፣ ሰሜን ወሎ ዞን | 31,660 | £75,230.00 |

የጤና ሚኒስትርም ገንዘቡ ወደ ባንክ አካውንቱ መግባቱን ያረጋገጠበትና በቀጣይ ገንዘቡ ለታለመለት አላማ መዋሉን የሚገልጽ ሪፖርት ክትትል በማድረግ እንደሚገልጽ ያሳወቀበትን ደብዳቤ ከዚህ ጋር አባሪ መደረጉን እየገለጽን ልገሳውን ላደረጋችሁ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት እና ከኤምባሲው ጋር በመሆን የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞቹን ላስተባበራችሁ ሁሉ ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ፋሪድ መለስ ደስታ
ልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ
ስልጣን አምባሳደር

Embassy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia LONDON

አባሪ ፡ የተጠቀሰው

ጤና ሚኒስቴር-ኢትዮጵያ
የዜጎች ጤና ለሀገር ብልፅግና!

Ministry of Health - Ethiopia
Healthier Citizens for Prosperous Nation!

ቀን 26/11/2014
Date

ቁጥር 4/AS/28/25
Ref. No.

ለክቡር አምባሳደር ተፈሪ መለሰ
ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤንባሲ ለንደን
<u>ለንደን</u>

ጉዳዩ:- <u>ከዲያስፖራዉ የተሰበሰበ ገንዘብ ወደ አካውንታችን መግባቱን ስለማሳወቅ፤</u>

ሚሲዮናችሁ በቀን 21/11/2014 ዓ.ም ቁጥር ኢ.አም.ለ. 757/4/4/8/2014 በጻፈው ደብዳቤ በ2014 በጀት ዓመት በዩናይትድ ኪንግደምና ሰሜን አየርላንድ የሚገኙ የዲያስፖራ አባላትን በማስተባበር በሀገራችን በተከሰተው ጦርነት ምክንያት የተጎዱ የጤና ተቋማትን መልሶ ለማቋቋም የሚያግዝ 291,730.26 (እንግሊዝ ፓውንድ ሁለት መቶ ዘጠና አንድ ሺህ ሰባት መቶ ለ26/100) በቁጥር 4/23/AS//28 በቀን 19/11/2014 ዓ.ም በጻፍንላችሁ ደብዳቤ መሠረት ማስተላለፋችሁን አሳውቃችሁናል።

በመሆኑም ወደ አሳወቅነው የሂሳብ ቁጥር ብር **18,345,107.32** /አስራ ስምንት ሚሊዮን ሶስት መቶ አርባ አምስት ሺህ አንድ መቶ ሰባት ከ32/100/ ብር ገቢ መሆኑን እየገለጽን የባንክ ማረጋገጫውን ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገናል። ጤና ሚኒስቴር ለተደረገለት ድጋፍ የላቀ ምስጋናውን እያቀረበ ገንዘቡን ለታለመለት አላማ በማዋል ስራውን ስናጠናቅቅ በሪፖርት የምናሳውቃችሁ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

ሊያ ታደሰ (ዶ/ር)
ሚኒስትር

ግልባጭ/

- ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
- ለኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት
  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት /ስርአት አቅም ግንባታ ዘርፍ/
- ለመድ/የሕክ/መሣሪ/አስ/ ዳይሬክቶሬት
  <u>ጤና ሚ/ር</u>


+251-115-517011
+251-115-518031
+251-115-159657
+251-115-524549
+251-115-516378
+251-115-513301
Fax +251-115-519366
1234
Addis Ababa, Ethiopia
E-mail: moh@moh.gov.et
Website: www.moh.gov.et
Ministry of Health, Ethiopia
@FMoHealth


አባክዎን መልስ ሲሰጡ የእኛን ደብዳቤ ቁጥር ይጥቀሱ
In Reply Please Refer to Our Ref.No.